የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

ከህዳር 4-ህዳር 10፣2017ዓ.ም
(November 13-19/2024)
Week Two

### 1.የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ላኪዎች የያዙትን ምርት እንዲሸጡ ማሳሰበያ ሰጠ

*ሪፖርተር፡ November 17, 2024*

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ምርት መሰብሰቢያ ወቅት ስለደረሰ፣ ላኪዎች የያዙትን ምርት በአስቸኳይ አውጥተው እንዲሸጡ ማሳሰቢያ ሰጠ፡፡

ሚኒስቴሩ ይህንን የገለጸው ከኢትዮጵያ ጥራጥሬና ቅባት እህሎች ምርት ላኪዎች ማኅበር ጋር 13ኛውን ዓለም አቀፍ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ኮንፈረንስ ለማካሄድ ዝግጅት ማጠናቀቁን አስመልክቶ፣ ዓርብ ኅዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ነው፡፡

የሚኒስቴሩ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ወጪ ንግድ ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ ወ/ሮ ያስሚን ወሐረቢ እንደገለጹት፣ ወቅቱ የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን መሰብሰቢያ ጊዜ ስለሆነ ላኪዎች ምርታቸውን በአስቸኳይ አውጥተው መሸጥ ይኖርባቸዋል፡፡

ላኪዎች የቆየውን ምርት በአፋጣኝ ወደ ገበያ አውጥተው በመሸጥ፣ አዲስ ምርት አስገብተው በውጭ ምንዛሪም ሆነ በውስጥ ንግድ ያለውን አፈጻጸም አሁን ካለበት ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲያሳድጉ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

በሩብ ዓመቱም 6.3 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ወደ ውጭ በመላክ 1.5 ቢሊዮን ብር ዶላር ገቢ መገኘቱን ጠቅሰው፣ ይህም ውጤት ሊመጣ የቻለው ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ ጀምሮ ምርትን በጥራት በዓለም አቀፍ ገበያው በማድረስ የተገኘ ውጤት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

የወጪ ንግድ ምርቶችን በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመቅረፅ፣ ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ ገበያ የምታቀርበው ምርት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135482/

### 2. ከከፍተኛ ማዕድን አልሚዎች የመንግሥት አምስት በመቶ ድርሻ አለመሰብሰቡ በክዋኔ ኦዲት ተረጋገጠ

*ሪፖርተር፡November 17, 2024*

በከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ከሚያመርቱ ባለፈቃድ ኩባንያዎች መንግሥት ማግኘት የነበረበት የአክሲዮን ድርሻ (ሮያሊቲ) እንዳልተሰበሰበ፣ በክዋኔ ኦዲት መረጋገጡን፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በ2015/16 በጀት ዓመት በማዕድን ሚኒስቴር የሚሰበሰበውን ገቢ በተመለከተ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መነሻ ላይ ውይይት ሲደረግ ነው ይህ የተገለጸው፡፡

ለክዋኔ ኦዲት ለናሙና ከተወሰዱ 50 የማዕድን ኩባንያዎች ውስጥ ከ31 ያህሉ የመንግሥት አክሲዮን ድርሻ የማዕድን ሚኒስቴር አለመሰብሰቡ መረጋገጡን፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ምክትል ዋና ኦዲተር አቶ አበራ ታደሰ ተናግረዋል፡፡

በከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ላይ የተሰማሩ ባለፈቃድ አምስት እጅ (አምስት በመቶ) የመንግሥት አክሲዮን ድርሻ (ሮያሊቲ)፣ የገቢ ግብር፣ የአካባቢና የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ (CDF) መክፈላቸውን የማዕድን ሚኒስቴር አለማረጋገጡን በክዋኔ ኦዲት መታወቁን ገልጸዋል፡፡

ምክትል ዋና ኦዲተሩ እንዳሉት፣ በ2013 በጀት ዓመት ማዕድን ከሚያለሙ ኩባንያዎች ምንም ዓይነት የመንግሥት አክሲዮን ድርሻ አልተሰበሰበም፡፡

ከ2014 እስከ 2016 ዓ.ም. የመንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ክፍያ በተበጣጠሰ መንገድ መሰብሰቡን በክዋኔ ኦዲት መረጋገጡንና የትርፍ ግብርን በተመለከተ የማዕድን ሚኒስቴር ‹‹ኩባንያዎች ከፍለዋል፣ አልከፈሉም›› የሚለውን መረጃ በአግባቡ እንዳልያዘ ገልጸዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135480/

### 3. ረቂቅ አዋጁ የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ላይ የሚስተዋለውን የብክነትና ህገ ወጥነት ችግር ለመፍታት ያስችላል

**ኢዜአ፡ ህዳር 9/2017**

የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣው ረቂቅ አዋጅ የነዳጅ አቅርቦት ፣ ስርጭት እና አጠቃቀም ላይ የሚስተዋለውን ብክነትና ህገ ወጥነት ችግር ለመፍታት የሚያስችል መሆኑ ተገለፀ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ በወጣው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከአስረጂዎች ጋር ተወያይቷል፡፡

ምክር ቤቱ ሰኔ 4 ቀን 2016ዓ.ም ባካሄደው ሶስተኛ የስራ ዘመን 31ኛ መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ስርዓት ለመደንገግ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ለዝርዝር እይታ ለቋሚ ኮሚቴ መምራቱ ይታወሳል።

ይህንንም ተከትሎ በተቀመጠው የምክር ቤቱ አሰራር መሰረት ቋሚ ኮሚቴው በዛሬው እለት በረቂቅ አዋጁ ላይ ጥያቄዎችን በማንሳት የአስረጂ መድረክ በማዘጋጀት ውይይት አድርጓል።

በውይይቱም ከዚህ ቀደም የነበረው አዋጅ 838/2006 የነዳጅ አቅርቦትና ግብይት እንዲሁም ስርጭት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5477288

### 4.ኮሪያ ሪፐብሊክ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የንግድ ልውውጥና የዲጂታል ግብይት ሥርዓት መደገፍና ማጠናከር ትፈልጋለች-አምባሳደር ካንግ ጁንግ

**ኢዜአ፡ ህዳር 9/2017**

ኮሪያ ሪፐብሊክ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የኢንቨትመንት፣ የንግድ ልውውጥና ዲጂታል የግብይት ሥርዓት መደገፍና ማጠናከር እንደምትፈልግ በኢትዮጵያ የኮሪያ ሪፐብሊክ አምባሳደር ካንግ ጁንግ ተናገሩ፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)፥ በኢትዮጵያ የኮሪያ ሪፐብሊክ አምባሳደርን በቢሯቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።

በዚህም ወቅት፥በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ማጠናከር፣በኢንቨትመንትና በንግድ ልውውጥ ያለውን ግንኙነት ማሳደግ ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሂዷል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) የኢትዮጵያና የኮሪያ ሪፐብሊክ ግንኙነት ታሪካዊ ነው ብለዋል።

አክለውም፥በኮሪያ ጦርነት ወቅት የኢትዮጵያ ወታደሮች የኮሪያን ህዝብ በመወገን ተዋግተው የደም ዋጋ የከፈሉ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

ኢትዮጵያ የቡናና የቅባት እህል ወጪ ምርቶችን ወደ ኮሪያ ሪፐብሊክ ገበያ እንደምትልክ ገልጸው፥ ኢትዮጵያ ከኮሪያ ሪፐብሊክ ጋር ያላትን የኢንቨትመንት አማራጮችንና ዕድሎች ለአምባሳደሩ ገልጸዋል።

በመሆኑም የሀገሪቱ ባለሀብቶች ያሉትን ምቹ ሁኔታዎችን ተጠቅመው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ የወሰደችው አገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ፈጣን እድገት ማስመዝገቡን የገለጹት ሚኒስትሩ የኮሪያ ሪፐብሊክ በዲጂታል ንግድና ግብይት ልምድ ያላት ሀገር በመሆኗ በኢኮሜርስና ዲጂታል ዘርፍ አቅም ግንባታና የልምድ ልውውጥ ድጋፍ እንድታደርግ ጠይቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ የኮሪያ ሪፐብሊክ አምባሳደር ካንግ ጁንግ፥ኮሪያ ሪፐብሊክ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የኢንቨትመንት፣ የንግድ ልውውጥና ዲጂታል የግብይት ሥርዓት መደገፍና ማጠናከር እንደምትፈልግ መናገራቸውን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5475877

**5. Tax officials pin compliance hopes on new QR code requirement**

**Reporter: November 16, 2024**

Officials at the Ministry of Revenues have issued a directive requiring all tax invoices to feature unique quick response (QR) codes in a bid to enhance tax compliance and transparency.

The amended tax invoice usage and administration directive mandates taxpayers to utilize differing invoices for each business category that applies to them, as well as for each business location, and include a unique QR code on the invoice.

Tax officials will not accept invoices that do not include this code, according to the directive inked by Aynalem Nigusie, minister of Revenue.

Starting immediately, all printing enterprises are required to include a unique QR code, provided by the tax authority, on every printed tax invoice. Officials hope the new rules will enhance tax compliance and streamline the verification process for tax authorities by ensuring the accurate tracking and reporting of transactions.

https://www.thereporterethiopia.com/42602/

**6. Trade Ministry clamps down on cement, fuel industries with strict new rules**

**Reporter: November 16, 2024**

Officials at the Ministry of Trade and Regional Integration have introduced new directives to regulate fuel distribution and improve cement production. The measures include a requirement for cement factories to operate at 80 percent capacity or face closure.

The regulatory changes were announced while Trade Minister Kassahun Gofe (PhD) presented his office's quarterly performance report to the Parliamentary standing committee for Tourism and Trade Affairs this week.

The committee criticized the Ministry's inefficiency in stabilizing markets, particularly in cement distribution.

Kassahun conceded that three previous directives aimed at resolving misconduct in cement distribution had failed, exacerbating existing problems. He attributed this failure to the Ministry's lack of capacity to implement and monitor the directives effectively.

https://www.thereporterethiopia.com/42599/#google_vignette

**7. Ethiopian Achieves Four-Star Global Airline Award**

**ENA; November 18/2024**

Ethiopian Airlines, Africa's leading aviation group, announced its recognition as the recipient of the Four-Star Global Airline award at the 2025 APEX Passenger Choice Awards.

This accolade highlights Ethiopian Airlines' unwavering commitment to delivering a service that meets global standards to its passengers across more than 140 international destinations.

As a SKYTRAX four-star global airline, Ethiopian attained this honor at the 2025 APEX Passenger Choice Awards, further reinforcing its reputation as a customer-centric service provider.

"We are truly honored to receive the prestigious 'Four-Star Global Airline' title once again," said Mesfin Tasew, CEO of Ethiopian Airlines Group.

This award underscored Ethiopian Airlines' determination to uphold the highest levels of service he said, adding "we are thrilled to have our efforts recognized once more, motivating us to strive for even greater achievements."

For the 2025 Awards, over one million Passenger Name Record (PNR) verified flights were rated by passengers across more than 600 airlines globally, utilizing a five-star scale.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5476272

**8. Ethiopia Hosts International Conference on Financing for Development in Africa**

**ENA: November 18/2024**

Ethiopia is hosting the regional consultation for the Fourth International Conference on Financing for Development in Africa. The consultation serves as a crucial event for African stakeholders to come together, align their views, and craft a unified African voice on critical issues related to financing development on the continent.

Ethiopia's State Minister of Finance, Semereta Sewasew, has officially opened the Regional Consultation for the Fourth International Conference on Financing for Development (FfD) in Africa.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5476223

**9. NBE to undergo major reorganization ahead of banking liberalization**

**Capital; November 18, 2024**

To ensure the stability of the financial system as it moves toward liberalization, the central bank, expected to receive the new establishment proclamation at the beginning of the New Year, will undergo institutional reorganization, including the establishment of new departments.

With the upcoming banking business proclamation, the central bank has clarified that it will not be deregulating the financial industry.

In recent appearances before Parliament, NBE Governor Mamo Esmelealem Mihretu addressed the two highly anticipated proclamations aimed at liberalizing the banking industry and enhancing the operations of the National Bank of Ethiopia (NBE). He stated that the regulatory body will reorganize its approach to drive the economy with a modernized system, facilitated by the changes in the NBE formation proclamation.

According to the draft proclamation, which is expected to be approved in the coming weeks, the central bank will establish a new committee. During a two-day session, which included a public hearing, Mamo outlined how the new proclamation will create a seven-member monetary policy committee. This committee will be responsible for developing and recommending monetary policy for the Board's approval.

https://capitalethiopia.com/2024/11/18/nbe-to-undergo-major-reorganization-ahead-of-banking-liberalization/

**10. Ethiopia urged to enhance policies to boost life insurance sector**

**Capital: November 18, 2024**

Ethiopia's life insurance sector is facing significant challenges, as industry leaders call for improved government policies to increase awareness and participation among citizens. Life insurance is designed to alleviate the financial burden on families following the death of a loved one by distributing funds to beneficiaries. However, the uptake of life insurance in Ethiopia remains low, with many individuals unaware of its benefits.

Despite Hibret Insurance's efforts over the past 30 years, the company reported only 232 million Birr in life insurance premiums for the 2023/24 fiscal year, a stark contrast to the total premium collection of 1.72 billion Birr, where non-life insurance operations dominate. Meseret Bezabih, CEO of Hibret Insurance, emphasized that while efforts have been made to promote life insurance, they have not resulted in substantial growth. "It is crucial for people to be informed about life insurance and for government policies to support its growth," she stated.

**https://capitalethiopia.com/2024/11/18/ethiopia-urged-to-enhance-policies-to-boost-life-insurance-sector/**